
# የእውነታ ሉህ ቁ. ፫

# በዘር ልዩነት ጦስ ድህነት በትምሕርት እና በመማር ላይ ያለው ተጽዕኖ

## የዘር ልዩነት ያላቸው ሰዎች በትምሕርት እና በመማር ላይ እንዴት ተጎድተዋል?

እ.ኤ.አ. በ2015 የጥቁር ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ምረቃ ቁጥሩ 69% ያህል ነበር፣ እንዲሁም ለነባር የአገሬው ተወላጅ ተማሪዎች 50% የነበረ ሲሆን ለነጮች ተማሪዎች ግን 84% ነበር። .




**መጉረፍ፡** ከነጭ ተማሪዎች ወይም በዘር ከተለዩ ከሌሎች ተማሪዎች ይልቅ ጥቁር እና ነባር የአገሬው ተወላጅ ተማሪዎች አካዳሚያዊ ወዳልሆኑ የትምሕርት ፕሮግራሞች እንደ ጅረት ይለቀቃሉ።

እ. ኤ. አ. በ2015 የቶሮንቶና አካባዋ ትምሕርት ቤት ቦርድ (ቲዲኤስቢ) ሪፖርት እንዳመለከተው 53% ጥቁር ተማሪዎች፣ እና 48% ነባር የአገሬው ተወላጅ ተማሪዎች፣ ነጭ ከሆኑት ጋር ሲነጻጸሩ የነጮቹ ተማሪዎች 81% በአካዳሚያዊ የጥናት መርሃ-ግብሮች ውስጥ ተመዝግበዋል፡

**በተግባረ-ዕድ** የትምሕርት ፕሮግራሞች ላይ 39% የጥቁር ተማሪዎች፣ እንዲሁም 41% ነባር የአገሬው ተወላጅ ተማሪዎች የተሰማሩ ሲሆን ከነጭ ተማሪዎች ደግሞ 16% ብቻ ነበሩ።
**መባረር:-** ጥቁር፣ ነባር የአገሬው ተወላጅ፣ እና የምስራቅ ሜዲተራንያን/ ደቡብ ምዕራብ ኤስያ ተማሪዎች ባልተመጣጠነ ቁጥር ከ ቲዲኤስቢ የመጀመሪያ ደረጃ/ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተባርረዋል። ይህም ከቲዲኤስቢ የተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት አሃዝ ጋር ሲነጻጸር ጥቁር ተማሪዎች 12% ሲሆኑ ከተባረሩት ጠቅላላ ደግሞ 48% የሚወክሉ ነበሩ። ነባር የአገሬው ተወላጅ ተማሪዎች ከጠቅላላው የተማሪዎች ቁጥር 0.3% ያህል የያዙ ሲሆን ነገርግን ከሚባረሩት መካከል 1% ያህል ይዘዋል። የምስራቃዊ ሜዲተራንያን / የደቡብ ምዕራብ ኤስያ ተማሪዎች ከጠቅላላ ብዛት 4% ሲሆኑ 8% የሚሆኑት ደግሞ የመባረር ዕድል ገጥሞአቸዋል።

**የፖሊስ ጥበቃ፡** ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል ተብለው የሚታሰቡ ትምሕርት ቤቶች ጥቁር ተማሪዎች በብዛት ያሉባቸው ሲሆኑ በትምሕርት ቤቶች ዙርያ የፖሊሶች ቁጥር እንዲጨምር ተደርጓል።

በቶሮንቶ ውስጥ የጸረ-አክራሪነት መርሃ-ግብሮች መግባት አስተማሪዎች በተማሪዎች መካከል የሚከሠት አክራሪነትን እንዴት በቀላሉ ማወቅና መለየት የሚችሉበት ሥልጠናን ያካተተ ነው። ድርጊቱም እስላም ተማሪዎች ላይ የሚደረገውን ስለላና የዘር ፍረጃን ሊየባብስ ይችላል።

**ፋኩልቲ**: እ. ኤ. አ. በ2016 የካናዳ የምርምር ጥናት ወንበሮች ፕሮግራም (CRC) ይህም ከፍተኛ ምሁራንን ለመሳብና ለማቆዬት የሚሠራ የካናዳ ፌደራል ኤጀንሲ ሲሆን ካናዳውያን ሴቶችን፣ የሚታዩ የአናሳ ብሔረሰቦች ተወላጆችን የሚወክሉ፣ የአካል ጉዳት ያላቸው፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲ ፋካልቲዎች የሚገኙ ነባር የአገሬ ተወላጆችን ለመቅጠር ያቀዱትን ዓመታዊ አገራዊ ግን ማሳካት አለመቻላቸውን የሚያሳይ መግለጫ አውጥቷል። የብዝሐ-ዓይነት [diversity] አመለካከት ማነስ ነባር የአገሬው ተወላጆችን እና የቀለም ተማሪዎችን ከብዙ ዕድል ይነጥላቸዋል፤ የእነርሱን ሞዴላዊ አርአያነት እና ምሳሌያዊ መካሪነት ያሳጣቸዋል። እንዲሁም ለማጥናት የሚፈልጓቸውን ርዕሰ-ጉዳዮች ይገድባቸዋል።

## ነባር የአገሬው ተወላጅ ላይ ትኩረት

እ. ኤ. አ. በ2011 በተደረገው ጥናት ከ 25 እስከ 64 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በካናዳ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች [First Nations] 27% ፤ ሜቲስ 17% ፤ እና 27% ኢኒዩት ሰርቲፊኬት ይሁን ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ አልነበራቸውም። በአንጻሩ ነባር የአግሬው ተወላጅ ያልሆኑት ግን 11% ነበር።




**ተከልሎ ከተመዘገበ ቦታ ውጭ ከሚኖሩት መካከል ¼ኛው የካናዳ ፈረስት ኔሽንስ እና ሜቲስ ሴቶች፣ እንዲሁም 38% ኢኒዩት ሴቶች የሁሉተኛ ደረጃ ትምሕርታቸውን ያለማጠናቀቅ ዋና ምክንያት ሆኖ ሪፖርት የተደረገው "እርግዝና / ሕጻናትን መንከባከብ" ነበር።**

በካናዳ ውስጥ 11% የሚሆኑት የአገሬው ተወላጅ ሰዎች የዩኒቨርሲቲ የምሥክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ በዲግሪ ደረጃም ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ሊሆኑ ይችላሉ። በአንጻሩ ግን ነባር የአገሬው ተወላጅ ያልሆኑቱ [የካናዳ] ዜጎች 29% ነበራቸው።

እ. ኤ. አ. በ2017 በካናዳ ከሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ምስክር ወረቀት ያላቸው 78.4% የአገሬው ተወላጅ ሰዎች ተቀጥረዋል። የአገሬው ተወላጅ ካልሆኑት ሰዎች ሲነጻጸር ደግሞ 86% ይሆናል።
የ2016 ሕዝብ ቆጠራ ከ2006 ጀምሮ በካናዳ ያለው የአገሬው ተወላጅ ሕዝብ ቁጥር በተመሳሳይ ጊዜ በ42.5% አድጓል። ይህም በተመሳሳይ ጊዜ የአገሬው ተወላጅ ካልሆኑት ሰዎች ቁጥር ከአራት ጊዜ እጥፍ በላይ መሆኑ ነው።

26% ነባር የአገሬው ተወላጅ ተማሪዎች- በአንጻሩ 47% የነጭ ተማሪዎች - በኦንታሪዮ ዩኒቨርሲቲ አመልክተው ተቀባይነት አግኝተዋል።

**ወላጆች በሠራተኞች በኩል የሚያሰቅቅና አክብሮት የጎደለው አያያዝ ያጋጥመናል። ምክንያቱም እኛ አፍሪካውያን ብቻ ሳንሆን በድህነትም የምንኖር ስለሆንን ነው። ለዚህም ሰዎች ከቆዳ ቀለም ጋር ድህነት ሲደመርበት ውጤቱ እንደ ደደብነት / ጅልነት አድርገው የሚመለከቱም አይጠፉም. . . በዘር ፍረጃ ግፍ ሲደረግብንና አክብሮትም ሲነፈገን እንደማናውቅና ወይም እንደማይገባን አድርገው የሚያስቡ ይመስላል።**



## ፈጣን ማስታወሻዎች

ስለ ቀለም ህዝቦች ስንነጋገር የዘር መሠረታችውና ቅሬተ-ቅርሳቸው ከአውሮፓ ያልሆኑትን ካናዳውያንን ማለታችን ነው።

እነዚህም ካናዳ ውስጥ የተወለዱና ከካናዳ ውጭ የትም የተወለዱ፣ በሁለቱም ጎራ ስላሉ የቀለም ሰዎች መናገራችን ነው።

ነባር የአገሬው ተወላጆች ስንል በአገሪቱ የነበሩ ቀድምት ህዝቦች {First Nations / Natives} [የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም ያልተመዘገቡ) ሜቲስ እና ኢንዩት ስለሚባሉ ሕዝቦች ነው። በቶሮንቶ ውስጥ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች ውስጥ 62% የሚሆኑት በዘር ልዩነት ከሚታዩ ቡድኖች ናቸው። በካናዳም በዘር ልዩነት ከሚታዩት ውስጥ 52% የሚኖሩት በኦንታሪዮ ውስጥ ነው።

በካናዳ ውስጥ በዝቅተኛ ገቢ ተቆራጭ (LICO) ወይም በዝቅተኛ የገቢ ልኬት (LIM) የሚመደቡ ቤተሰቦች ከገቢዎቻቸው ውስጥ በጣም ከመቶኛ ውስጥ ትልቁን የሚያጠፉት በአስፈላጊና መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ እና መጠለያ የመሳሰሉት ናቸው። ድህነትን የምንለካውም በዚህ መንገድ ነው።

ስልታዊ ዘረኝነት ብዙዉን በስውር በሚሠራ ተቋማዊና የተዛባ ፖሊሲ፣ ልምምድና አሠራር ምክንያት የሚፈጸም ሆኖ በተለያዩ ቡድኖች መካከል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ አሠራር ነው። የተወሰኑ ቡድኖችን በተለያዩ መንገዶች እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሁልጊዜም እንደተለመደው አካሄድ ብቻ የመከተል ውጤት ሊሆን ይችላል።

**ማንበብ፡-** ቲዲ ኤስ ቢ ባደረገው ጥናት መሠረት ዝቅተኛ ገቢ [በዓመት ከ $30,000 በታች ገቢ ያላቸው ቤተሰብ] ክሚመጡ ተማሪዎች 47% የክፍለ-ሀገሩን የንባብ መመዘኛ መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። ይህም ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ወላጆች ከሚመጡ ተማሪዎች (በዓመት 100,000 ዶላር ወይም ከዚያ በላይ የሚያገኙ ወላጆች) ጋር ሲነፃፀር 66% ይሆናል። (ያስታውሱ ፤ በቶሮንቶ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች 62% የሚሆኑት በዘር ልዩነት ዙርያ የሚመደቡ ናቸው)።

**ከፍተኛ ትምሕርት፡-** ገቢያቸው ዝቅተኛ ደረጃ ከሆነ ቤተሰብ የሚመጡ ልጆች ከፍተኛ የገቢ ደረጃ ካላቸው ቤተሰብ ከሚመጡ ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር ግማሽ ያህል ዩኒቨርስቲ ገብተው ይማራሉ።

**ማንበብና መጻፍ፡** ማኅበራዊ ድጎማ ከሚያገኙ ሰዎች መካከል 65% የሚሆኑት በካናዳ ማኅበረሰብ ውስጥ ለመሥራት የሚያስችል ተገቢ የማንበብና መጻፍ ችሎታ የላቸውም።

**ሥርዓተ-ትምሕርት፡-** የአገሬው ተወላጅ ሕዝቦችና የቀለም ማሕበረሰቦችን ታሪክና አስተዋጽኦን ወደ ጎን ተጥሎ
ሥርዓተ-ትምሕርቱ የ"ነጭ-ማዕከልነትን" ይዞ እየቀጠለ ይገኛል።

**የሕጻናት ድህነት፡-** የአገሬው ተወላጅ ልጆችና የስደተኞች ልጆች የሕጻናት ድህነት መጠን ከፍ ያለ ነው።

**በካናዳ የሕጻናት ድኅነት መጠን ሲለካ ስደተኛ ያልሆኑ ነጮች ሕጻናት ልጆች 13% ሲሆን ነገር ግን ለአገሬው ተወላጅ ልጆች 51% ነው። (እንዲሁም በህግ በተከለለ ቦታ የሚኖሩ የአገሬው ተወላጅ ሕጻናት ልጆች 60%)፤ የስደተኞች ልጆች 32% ፤ የቀለም ልጆች ደግሞ ከአጠቃላዩ ሲታይ 25% ይሆናል።**




# ምን እየተደረገ ነው?

የኦንታሪዮ የጸረ ዘረኝነት ማልቲካልቸራል ትምሕርት አውታረ-መረብ [ኤኤምኢኤንኦ] ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ከአስተማሪዎች፣ ማኅበረሰባዊ አባላት፣ እንዲሁም ኢ-ፍትሐዊነትንና መገለልን ለመዋጋት ከተነሳሱ ወላጆች የተሰባሰበ ቡድን ነው።

ስለ ፍትሃዊነት ጉዳዮችና መርሃ-ግብሮች ድጋፍ ለማሰባሰብና እንዲሁም የሕዝብን ትምሕርት ለመደገፍ የግኑኝነት አውታረ-መረብ ዘርግተዋል፦
www.ameno.ca / info@ameno.ca

ካናድያን ሩት ኤክስቸንጅ የሚባለው ደግሞ መሠረቱ በኦንታሪዮ ያደረገና የአገሬው ተወላጅ ሰዎች (ኢንዲጂንዮስ) የሚመሩት ሆኖ የአገሬው ተወላጅ ለሆኑና ላልሆኑ ወጣቶች የተሞክሮአዊ ልምድ ዕድሎችን የሚሰጥ ድርጅት ነው።

ለምሳሌ አንድ ላይ በሚገናኙበት ጊዜ ባህል-ዘለል ግንዛቤንና እርቅን ለመስጠት፣ ለመማር፣ ገለጻ ለማድረግ እና ስለ ባህላዊ ጉዳዮች ጥብቅና ቆሞ ለመሟገት ኮንፈረንስና የልምድ ልውውጦችን የማድረግ ሀሳብ ነው፦
www.canadianroots.ca / info@canadianroots.ca